# የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ)

**Ethiopian People's Congress for United Struggle (Shengo)**

www.ethioshengo.org shengo.derbiaber@gmail.com


የካቲት 7 ቀን፣ 2008 (ፌበርዋሪ 15፣ 2016)

## የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) የአመራር ምክር ቤት መደበኛ ጉባኤ አካሄደ የወቅቱን ሁኔታ ገምግሞ የጋራ ትግሉን ለማጠናከር ተጨማሪ መመሪያ ሰጠ

የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) የአመራር ምክር ቤት ቅዳሜ ጥር 28፣ 20008 (ፌበርዋሪ 6፣ 2016) መደበኛ ጉባኤውን አካሂዷል። በዚህ ጉባኤው ምክር ቤቱ ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትገኝበትን ሁኔታ፣ በህዝባችን ትግል አኳያ የሚታዩትን ተስፋ ሰጭ ገጽታወችና አሳሳቢ ክስተቶችን በሰፊው ገምግሟል፡ ፤ የሸንጎ የተለያዩ የስራ ክፍሎች የሚያካሆዱትን ተግባር በተመለከተ የቀረቡትን የስራ ሀገባወች መርምሯል። በመቀጠልም በህዝበችን ላይ እየደረሰ የሚገኘውን ግፍ ሊያከትም እንዲችልም መካሄድ በሚገባው ትግል ላይ አስፈላጊውን የተግባር መመሪያወች ሰጥቷል፤ የትግል ጥሪም አስተላልፏል።

የ25 አመቱ የህወሀት/ኢህአዴግ አምባገነን የግፍ ስርአት ኢትዮጵያን አደጋ ላይ ጥሏል። ኢትዮጵያውያንን አስመርሯል። በሁሉም የሀገራችን ክፍል የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ህገ መንግስታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እውን የሚሆንበትን ጊዜ ናፍቋል። መናፈቅ ብቻም ሳይሆን፣ አንድነቷ በተጠበቀ ኢትዮጵያ ስር መብቱን ለማስከበር፣ የህግ የበላይነትን እውን ለማድረግ፣ ከፋፋይ ስርአትን ለማስወገድ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በየቦታው ተቃውሞውን በተለያየ መልክ በመግለጥ ላይ ይገኛል። ህዝባችን በተለያየ የሀገሪቱ ክፍል መብቱን ለማስከበር ከፍተኛ መስዋእትነትን በመክፈል ላይ ነው። ስርአቱ በመፍረክረክ ላይ ይገኛል፣ክንዱ ዝሏል። አደንቋሪ ፕሮፓጋንዳው የሚያዳምጠው ጆሮ አጥቷል። በሀገራችን ውስጥ ያለው ሁኔታ የሚያሳየው ሀገራችን የለውጥ ዋዜማ ላይ መሆኗን ነው።

በዚህ አኳያ በአሁኑ ሰአት በመላ ሀገራችን በተለይም ደግሞ ኦሮሚያ፤ አማራና ጋምቤላ ተብለው በሚታወቁት ክልሎች እየተካሄደ ያለውን የመብት ማስከበር ትግል፣ የመሬት ቅርምትንና ዘረፋ የመቃወም ትግል ፣ አግላዩን የፖለቲካ ስርአት በመቃወም፣ የሚደረገውን ትግል የመሰረታዊ መብት መገፈፍን፤ በቃኝ በማለት የስርአቱን ጨቋኝ አገዛዘ እንዲወገድ የሚደረገውን ትግል፣ ስርአቱ በተከታታይ የሚያካሂደውን ህዝብን የእርስ በርስ የማጋጨት ተግባር በመቃወም የሚደረገውን የህዝብ እንቅስቃሴ ሸንጎ ካሁን በፊት እንዳደረገው ሁሉ አሁንም ይደግፋል፣ የትግል አንድነቱንም ይገልጻል።

ስርአቱ ለዚህ የህዝብ ትግል ተገቢ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ እንደተለመደው በማን አለብኝነት ለማፈን የሚወስደውን የሀይል እርምጃ፣ እስራት፣ ድብደባና ግድያ ምክር ቤቱ እንዳለፉት ጊዜያት ሁሉ አሁንም ያወግዛል። በደል ለደረሰባቸው ሁሉም የሀዘናቸው ተካፋይነቱን ይገልጣል። ከዚህ ሁኔታ ጋር ተያይዞም የታሰሩት ሁሉ ባስቸኳይ እንዲለቀቁ ንብረታቸው ለጠፋው እንዲሁም በስርአቱ የጸጥታ ሀይሎች ለተገደሉ አስፈላጊው ህጋዊ ካሳ ለቤተሰቦቻቸው እንዲከፈልና ገዳዮቹም ሆኑ ትእዛዝ ሰጭዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ ለማድረግ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ትግሉን እንዲቀጥል ምክር ቤቱ ጥሪ አቅርቧል።

ከዚህ ጋር በተያያዘም ይህን የህዝብ ትግል ለጠባብና ከፋፋይ አላማ ሊያውሉት የሚጥሩትን አንዳንድ የውስጥም የውጭም ሀይሎች እንዲሁም የስርአቱን ደባ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በጥንቃቄ ነቅቶ እንዲከታተልና የከፋፋዮች ሰለባ እንዳይሆንም፡ ነቅቶ እንዲጠብቅ አሳስቧል።


Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : shengo.derbiaber@gmail.com

የህዝባችንን የትግል መነሳሳት ወደተፈለገው የስርአት ለውጥ እንዲያመራ የተቃዋሚው ወገን ታላቅ ሀላፊነት እንዳለበትና በተናጠል የሚደረግ ትግል ለስርአቱ እድሜ መራዘም የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በመገንዘብ ይህን ሁኔታ ለመቀየር የሚያስችል አስተማማኝና ቀጣይ ትግል ለማካሄድ ከሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር በጋራ ለመስራት በሸንጎው በኩል የሚደረገውን ጥረት ከመረመረ በኋላ የተጀመረው ጥረት ተጠናክሮና ቅድሚያ ተሰጥቶት እንዲቀጥል፣ ሌሎች የአንድነት ሀይሎችም የጋራ ትግሉን እውን ማድረግ አጣዳፊነት ተረድተው ጠንካራ የተቃዋሚ ህብረት በመመስረቱ ተግባር ላይ በጋራ መረባረብ ይገባቸዋል ሲል ምክር ቤቱ ለሁሉም የአንድነት ሀይሎች የትብብር ጥሪውን በድጋሚ አስተላልፏል።

የህወሀት/ ኢህአዴግ አምባገነን ስርአት ዕለታዊ ተግባር በሀገሪቱ ውስጥ ሰላምና መረጋጋት እንዲጠፋ እያደረገ እንደሆነ አለም አቀፍ ህብረተሰቡ ተገንዝቦ ይህን አደጋ ለማስወገድም የኢትዮጵያ ህዝብ ለመሰረታዊ መብቱ መከበርና ፣ ለህግ የበላይነት የሚያካሂደውን ትግል እንዲያግዝ ከምን ጊዜውም የላቀ ዲፕሎማሲያዊ ትግል እንዲካሄድ ምክር ቤቱ ተጨማሪ መመሪያ ሰጥቷል።

በመጨረሻም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ለመሰረታዊ ጥያቄዎቹ መልስ ማግኘት ማለትም ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር፣ ራሱ የመረጠውና የሚቆጣጠረው መንግስት ለመመስረት፣ ለህግ የበላይነት መከበር፣ የከፋፋይ ስርአት እንዲያከትም የፖለቲካ ስርአቱ ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ ሙሉ ተሳታፊ የመሆን መብቱ እንዲከበር፣ በነጻነትና ያለፍርሃት መኖር እንዲችል የኢኮኖሚ ተስፋ፣ የማህበራዊ ፍትህ ፣ እውን እንዲሆን ሁሉም ዜጋ ማንነቱ ተከብሮ በቋንቋው የመጠቀም፣ ባህሉን የማዳበር፣ መብቱ ተጠብቆ መኖር...ወዘተ እንዲችል ለሚደረገው ትግል ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትግል አጋርነቱን እንዲገልጥ የአንዱ ኢትዮጵያዊ መጠቃት የሌላው መጠቃት እንደሆነ በመገንዘብ እጅ ለእጅ በመያያዝ በተባበረ ትግል የጭቆናውን ስርአት ለማስወገድና ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በእኩልነት የሚያስተናግድ ህገ-መንግስታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመመስረት በጋራና በመተጋገዝ እንዲታገል የሸንጎው የአመራር ምክር ቤት ጥሪ አድርጓል።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ

Tel: 44 7937600756 , +1 9168486790 E-mail : **shengo.derbiaber@gmail.com**